# የተደናገጠው ወያኔ እና ጀሌዎቹ

ከኃይለ ልዑል ግርማ(ዋሽንግተን ዲሲ)

የሕዝብ ትግል ሲጠናከርና እንቅስቃሴ ሲካሄድ የወያኔ ባለሥልጣኖች እንቅልፍ ያሳጣቸዋል፣ ካድሬዎቻቸው ይደናገጣሉ፣ ደጋፊዎቻቸው ይርበተበታሉ። ይህንን ደግሞ ለመሸፈን የተፈጠሩበት አረመኔ ባህሪያቸው እያገረሸባቸው የለመዱትን ሕዝብ የማሰቃየት፣ የማሰር፣ የመደብደብ እና የማዋረድ ስራቸውን በጠራራ ጸሐይ ያደርጉታል። ሲቻላቸውም በፊት ለፊትና በድብቅ የንጹሐንን ደም ያፈሳሉ። በዚህም የሕዝብን ትግል ያዳፈኑ፣ ያፈኑ፣ እና የገቱ ይመስላቸዋል። በጭራሽ ከታሪክ አይማሩም። መማርም አይፈልጉም። ለዚህም ነው ሰሞኑን በመላው አዲስ አበባ የተደረገው የመኢአድ ሰላማዊ እንቅስቃሴ አስደንግጧቸው ወጣቶችን በማሰርና በመደብደብ፣ ጥርስ በማውለቅ፣ በማንገላታትና ድጋፍ የሰጣቸውን ሕዝብ በመደብደብ እንቅስቃሴውን ለመግታት የሞከሩት። ሕዝብ ግን ድጋፉን በእልልታና በጭብጨባ በማጀብና ቅስቀሳውን በማዳመጥ ድጋፉን ሰጥቷቸዋል። በሶስቱም ቀናቶች ፖሊሶች ጣልቃ በመግባት ለማስቆም ሞክረዋል። የአንድ የፖሊስ ኃላፊ ባለሥልጣን ደግሞ የመኢአድ ወጣቶች የያዙትን የኢትዮጵያ ስንደቅ ዓላማ ከመኪናው ላይ በመግፈፍ (የወያኔ ሰማያዊ ቀለም ያለበት አርማ ስለሌለው) እንደጣለውና በእግሩ እንደረገጠው፣ የመኢአድን ፕሬዚዳንት ፎቶግራፍ በመግፈፍና በመቀዳደድ መጣሉ እንዲያውም በእጃቸው ላይ አስረውት የነበረውን አረንጓዴ ብጫ ቀይ የእጅ ባንዲራና /ባንድ/ አውልቆ መውሰዱ ቢገርመንም የተከበረችው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ መሆኗን ግን መገንዘብ አልቻለም።

ከምርጫ 97 ወዲህ የወያኔ የደህንነት ማፈኛ ክፍል፣ የፖሊስ፣ የተለያዩ ባለሥልጣኖች፣ ካድሬዎችና ተላላኪዎቻቸው ያተኮሩትና ሲሰሩበት የቆዩበት አንዱ ነገር፤ የሚያዝያ 30ው 97 ዓይነት የሕዝብ እንቅስቃሴና ድጋፍ ዳግም እንዳይታይ፣ እንዳይኖር ማድረግን ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ የቅንጅትን አመራር በሰርጎ ገቦቻቸው አማካኝነት ማፈራረስና ቅንጅትን ማጥፋት ነበር። አዎን ቅንጅት የሚለውን ስም ለመከልከል የቻሉ መስሏቸው ይሆናል። ቁም ነገሩ ከስሙ ላይ ሳይሆን ከዓላማውና ከተግባሩ ስለሆነ የቅንጅት ተወካዮች በሰኔ 14 እና 15 2000 ዓ.ም ተሰብስበው ተነጋግረው አመራራቸውን መርጠው፣ በቅንጅት ስም ላይ ውሳኔ አስተላልፈው እንደነበር ይታወሳል። በፍርድ ቤትም የሚችሉትን ያህል ተሟግተውና ተከራክረው ነበር። የቅንጅት ስምም በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት መለወጡን አስታውቀው ወደ ጀመሩት የማደራጀትና የማጠናከር ስራ ላይ ተሰማርተዋል።

ቅንጅት ወይም የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ሥራውን ሲሰራ አባላቱ እየታሰሩ፣ በጥይት እየተመቱ፣ በዱላ እየተደበደቡ፣ ንብረታቸው እየተወረሰ፣ ቤታቸው እየፈረሰ በከፍተኛ መስዋዕትነት በጀግንነት በመታገል ላይ ሲሆኑ፤ ይህንን ከፍተኛ መስዋዕትነት እየተከፈለበት ያለውን ትግል ለማፈን ሁለት ፊት ዘመቻ እየተካሄደበት ይገኛል። በአንድ ፊት የየአካባቢው የወያኔ ባለሥልጣኖችና ካድሬዎች የሚያደርሱባቸው ቀጥተኛ ወከባ፣ ድብደባ፣ እስራትና ስቃይ ነው። የወያኔ ባለሥልጣኖች ሕገ መንግሥቱ የሚፈቅድላቸውን መብት በመግፈፍ፣ ሕጋዊ እንቅስቃሴያቸውን ሕገወጥ እያሉ በአምባገነንነት ሕገወጥና አረመኔያዊ ተግባራትን ቢፈጽሙባቸውም፤ የመኢአድ አባላትና ደጋፊዎች መብታቸውንና ዓላማቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ስለሆነ ያለምንም ፍርሃትና

ማመንታት የሚደርስባቸውን ሁሉ ስቃይ ከምንም ሳይቆጥሩ ሰላማዊ ትግላቸውን ቀጥለዋል፡፡ የወያኔ ባለሥልጣኖች የሕዝብን ትግል ለማፈን የሚያደርጉት መፍጨርጨር ከውድቀትና ከተጠያቂነት የሚያድናቸው አይደለም ይበልጥ ተጠያቂና ወንጀለኛ ያደርጋቸውል እንጂ፡፡ በዚህም የውድቀት ቀናቸውን ያፋጥናሉ፡፡

ሌላው በዚህ የሕዝብ እንቅስቃሴ የተደናገጡትና የተረበሹት ደግሞ በተቃዋሚ ስም የቅንጅትን ትግል ለመጥለፍ ያደጉት ሙከራ ባይሳካም ከፍተኛ ጉዳትና ችግር ፈጥረው የነበሩት "የቅንጅት ወራሽ ነን" እና "ሁለገብ ትግል ብቻ ነው መፍትሔው" የሚሉት የቅንጅት አፍራሾች ናቸው፡፡ እነዚህ ከመሰረታቸውም የሕዝብን ትግል ለማፈን የተፈጠሩት እና በሆዳቸው በተገዙ ጥቂት ደጋፊዎቻቸው አማካኝነት ከዚህ ቀደም በቅንጅት ስም የሰበሰቡትን ገንዘብ ምን እንዳደረጉ ካለመታወቁም በላይ፣ መኢአድ ያደራጃቸውን አባላቱን በገንዘብ ለመደለል ያደረጉት ከንቱ ሙከራ እና እንቅስቃሴውን ለማክሸፍ የሚያደርጉት ያልተሳካ ሙከራ ማንነታቸውን ግልጽ አደርጎ እያሳየ ነው፡፡ እነዚህ በምርጫ 2010 የፓርላማ ወንበር ተስፈኞች የሚያደርጉት አፍራሽ ሥራ በሕዝብ እንደሚከሽፍ መታወቅና መጋለጥ ይኖርበታል፡፡ ከነልደቱ አያሌው የክህደት ተግባር ተምረናልና ዛሬም "የልደቱ ወራሾች" ለመሆን የሚሯሯጡትን ጥቂት በውጭ አገሮች የሚገኙ የተገዙ ካድሬዎቻቸው እና ወዳጆቻቸው ይደግፏቸው እንደሆን እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነታቸውን አውቋቸዋል፡፡ እነርሱንም እንደ ተቃዋሚ ቆጥረው "አንድነት" ይፈጠር እያሉ የውሸት ከበሮ የሚደልቁ ካድሬዎቻው ዋና ዓላማ እነዚህ ትግሉን የከዱት "የአንድነት ፓርቲና" "የግንቦት 7 ድርጅትን" መሰሪና አፍራሽ ዓላማቸውን ለመሸፈንና ለማደናገር የሚጠቀሙበት ስለሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህን የተንኮል መፈክራቸውን ሊገነዘበው ይገባል፡፡

ማን ከሕዝብ ጋር እንደቆመ ማን ደግሞ በተቃዋሚ ስም የወያኔን እድሜ ለማራዘም እየተሯሯጠ እንደሆነ እየታየ ነው፡፡ በውጭ ጠላቶቻችንና በወያኔ የስውር እርዳታ አማካኝነት ትግሉን ለመጥለፍና ለወያኔ ለማስረከብ የተሰለፉትን ምሁር ተብዬዎችና ለሆዳቸው በተገዙ፣ እንዲሁም በጠባበ የጎሳ አመለካከት ተሸብበው ሬዲዮኖች፣ ፓልቶክ ክፍልና ድኅረገጾችን እንደ አሸን አፍልተው ሲለፈልፉ ማንን ይዘው ለማን እንደሚታገሉ ደጋፊ ነን የሚሉ ሰዎች ማሰብና መመርመር ይኖርባቸዋል፡፡ "በሁለገብ ትግልና" "በሰላማዊ ትግል" እንታገላለን ያሉትም ሰዎች አንድ ላይ እንደሚሰሩ በተደጋጋሚ መጠቀሱ የሚታወስ ሲሆን አሁን ደግሞ ካድሬዎቻቸው የበለጠ እያጋለጡትና ግልጽ እያደረጉት መጥተዋል፡፡ በሰሞኑ የመኢአድ እንቅስቃሴ ተቃዋሚ ነን ባዮቹ እንደ ወያኔ ተደናግጠው ታይተዋል፡፡ ሴራቸው መክሸፉ ነዋ፡፡ ምናልባትም እነርሱም የዜና ሽፋን ለ ማግኘት ድራማ እንደለመዱት ቢሰሩ አይደንቀንም፡፡ የአውሮፖውም ሽርሽር ብዙም አል ተሳካ፡፡ የገንዘብ ችግር የለባቸው መላውን ዓለም ቢዞሩ አይገርምም፡፡ የሌላቸውና የማያገኙት የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ነው፡፡ ሕዝብ ካልደገፋቸው ደግሞ የማን መልዕክተኞች መሆና ቸውን ሕዝብ ያየውና እያወቀው መጥቷል፡፡ አዬ የወያኔ ጀሌዎች ማፈሪያዎች ሆነው ቀሩ፡፡

ስለሆነም በወያኔም ሆነ በወያኔ ጀሌዎች አማካኝነት የሚደረገው የመከፋፈልና የማፍረስ ሥራ በሕዝብ ትግል እንደሚከሽፍና ሁለቱንም ክፍል ማለትም ወያኔን እና ጀሌዎቹን ለሕዝብ ፍርድ እንደሚያቀርባቸው አይጠረጠርም፡፡

የሕዝብ ትግል ያሸንፋል!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!